# በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚታተሙ ደረሰኞች ሽልማት የሚያስገኝ ዕጣ እንዲኖራቸው ለማድረግ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ

**□□□□ □□□ 120/2013**

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*ነሐሴ 2001 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ*

# በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የሚታተሙ ደረሰኞች ሽልማት የሚያስገኝ ዕጣ እንዲኖራቸው ለማድረግ የወጣ የአፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 120/2013

ተጠቃሚዎች ወይም ሸማቾች ለሚያከናውኑት ግብይት ደረሰኝ በመጠየቅና በመቀበል ለግብር/ታክስ አሰባሰብ የሚረዳ መረጃ ለመሰብሰብ የሚደረገውን ሥራ ለማገዝ እንዲችሉ ደረሰኝ የመቀበል ባህል እንዲያዳብሩ የሚያደርግ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 አንቀጽ 22 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በሚመለከት ባወጣው መመሪያ ቁጥር 46/1999 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 33 በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎቹ የሚታተሙ ደረሰኞች ሽልማት የሚያስገኝ እጣ ኖሯቸው የዕጣውን አሸናፊ የሽልማት ተጠቃሚ ስለሚያደርጉበት ሁኔታ በዝርዝር መመሪያ እንደሚወሰን የተመለከተ በመሆኑ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ይህን የአፈጻፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የሚታተሙ ደረሰኞች ሽልማት የሚያስገኝ ዕጣ እንዲኖራቸው ለማድረግ የወጣ የአፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 120/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

**በዚህ መመሪያ ውስጥ፣**

1. **"የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ማለት"** የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ማለት ነው፡፡
2. **"ሽልማት የሚያስገኝ ዕጣ ያለው ደረሰኝ"** ማለት ስለ ደረሰኝ በደንቡ አንቀጽ 2(3) ላይ የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ ለተሸጠ እቃ ወይም አገልግሎት በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ታትሞ ለደንበኞች የሚሰጥ፣ ለአንድ ደረሰኝ የሚሰጥ ቁጥር በተመሳሳይ ለሌላ ደረሰኝ ሳይሰጥና ሳይደጋገም ተከታታይ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን እንዲሁም የመሳሪያው መለያ ቁጥር ያለው፣ የከፋዩን ስም ወይም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር

የሚያሳይ የክፍያ ማረጋገጫ ሲሆን፣ የደረሰኙ ቁጥር የዕጣው አሸናፊ ሆኖ ሲቀርብ ሽልማት ለማግኘት የሚያስችል ነው፡፡

3. **"ደንብ"** ማለት በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 ነው፡፡
4. **"ሽልማት"** ማለት የዕጣ አሸናፊ ቁጥሮች ለደረሳቸው ደንበኞች ወይም ሰዎች በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የሚደረግ ስጦታ ነው፡፡
5. **"ባለሥልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው፡፡
6. **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡
7. **"አዋጅ"** ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ናቸው፡፡
8. በዚህ መመሪያ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ቃላት ከተገኙ በአዋጆቹ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በደንቡ መሠረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ባለባቸው ሰዎች በተከናወነ ግብይት በተሰጠ ደረሰኝ ላይ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 4. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

ደረሰኝ በመስጠት ሽያጭን የማካሄድና ግዥ ፈጽሞ ደረሰኝ መቀበልን በማበረታታት አሠራሩ በሂደት ቋሚ ባህል ተደርጐ እንዲወሰድ በማስቻል በግብር ሰብሳቢው አካልና በግብር ከፋዩ መካከል በትክክለኛ መረጃ ወይም ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖርና የተሻለ የግብር አሰባሰብ እና የመረጃ ሥርዓት እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡

## 5. <u>ደረሰኞች ሽልማት እንዲያስገኙ ዕጣ እንዲኖራቸው ስለሚደረግበት ሁኔታ</u>

1. የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ያወጣው የፕሮሞሽን ውድድር ዝግጅት ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 2/1995 እንደተጠበቀ ሆኖ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የታተሙ ደረሰኞች ሽልማት ለማግኘት የሚያገለግሉት ባለሥልጣኑ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ የታተሙ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

2. በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚታተሙ ደረሰኞች የሚለዩበት እንደዚሁም እንደአስፈላጊነቱ የንግድ ዘርፍ ወይም የንግድ አካባቢን መሠረት በማድረግ የሚወጡ የደረሰኝ ሎተሪ ዕጣዎችን የመለየት ተግባር ኮምፒውተራይዝድ በሆነ የናሙና መምረጫ ዘዴ ይከናወናል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ደረሰኝን ሽልማት የሚያስገኝ ዕጣ እንዲኖረው አድርጐ ለመጠቀም የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የሚሰጠው ፈቃድ ይኖረዋል፡፡

## 6. <u>ሽልማት የሚያስገኝ የዕጣ ቁጥር</u>

1) ለደረሰኞቹ በቅደም ተከተል የሚሰጠው ቁጥር እና የመሣሪያዎቹ መለያ ቁጥር ሽልማት የሚያስገኝ የዕጣ ቁጥር ይሆናል፡፡ ተመሳሳይ የደረሰኝ ቁጥር በሌላ ደረሰኝ ላይ መደገምና መሰጠት የለበትም፡፡
2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ደረሰኝ የግብር ከፋዩን መለያ ቁጥር (TIN) እና የመሳሪያውን መለያ ቁጥር ወይም ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን የተለየ መለያና የደረሰኝ ቁጥር መያዝ ይኖርበታል፡፡

## 7. <u>የዕጣ ኘሮግራም የቆይታ ጊዜ</u>

1) የዕጣው አወጣጥ ኘሮግራም በባለሥልጣኑ በሚወሰነው የቆይታ ወይም የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሚከናወን ይሆናል፡፡
2) የሽልማቶች ዓይነትና መጠንም በባለሥልጣኑ በየጊዜው ተወስነው ይቀርባሉ፡፡

## 8. <u>ዕጣው የሚወጣበት ጊዜ</u>

1) የብሔራዊ ሎተሪ የሚሰጠው ፈቃድ እንደተጠበቀ ሆኖ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የሚታተም ሽልማት የሚያስገኝ ዕጣ ያለው ደረሰኝ ዕጣ አወጣጥ ስነ ስርዓት ባለሥልጣኑ በሚወስነው ቀን፣ በሚያወጣው ፕሮግራምና በየወቅቱ በመገናኛ ብዙሃን በሚገለፀው መሠረት ይካሄዳል፡፡
2) ዕጣው የሚወጣበት ቦታ፣ ጊዜና የሽልማቶቹ ዓይነት እና ብዛት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የህዝብ ማስታወቂያ ወይም በራሪ ወረቀት ወይም ፖስተር ወይም ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው ቋሚ የመለጠፊያ ቦታ ላይ ይገለፃል፡፡

## 9. ሽልማት የሚያስገኝ ደረሰኝ የዕጣ አወጣጥ ስነሥርዓት አፈፃፀም

ሽልማት የሚያስገኝ ደረሰኝ የዕጣ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ተጋብዘው በሚገኙበት በግልጽ የሚካሄድ ሲሆን ሥነ ሥርዓቱ ወይም ውጤቱ ወይም ሁለቱም በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ይተላለፋል፡፡

## 10. ለዕጣው አሸናፊዎች ስለሚሰጡ ሽልማቶች

1. የደረሰኝ ሎተሪ የዕጣ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት ከመካሄዱ ቢያንስ 15 ቀናት በፊት ጀምሮ የዕጣው አሸናፊ ቁጥሮች የሚያስገኟቸው ሽልማቶችና ዓይነታቸው በደረጃ ተለይተው /1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ … በሚል/ ለሕዝብ ይገለጻል፡፡
2. ከዚህ በላይ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የዕጣው አሸናፊዎች እና የሽልማት ዓይነቶች በማንኛውም የሕዝብ ማስታወቂያ፣ በራዲዮ፣ በቴሌቪዥን ወይም በጋዜጦች ለሕዝብ ይገለፃሉ፡፡
3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2(4) የተመለከተው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ ለአሸናፊ ቁጥሮች የሚሰጠው ሽልማት በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ይሆናል፡፡

## 11. የሽልማት አሰጣጥ

1. የገዢውን ስምና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ወይም ከሁለቱ አንዱን የያዘ አሸናፊ ደረሰኝ ሲቀርብ የስሙ ባለቤት ወይም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ባለቤት ለሆነ ሰው ሽልማቱ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ስም ወይም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሌለው ደረሰኝ ከሆነና ቁጥሩ አሸናፊ ሆኖ ከቀረበ ባለስልጣኑ በዕጣው አሸናፊ ለሆነው ቁጥር የተመለከተውን ሽልማት ወዲያውኑ ለአምጪው ይሰጣል፡፡

## 12. ሽልማት የማይሰጥበት ሁኔታ

1) ሽልማት የሚያስገኝ ደረሰኝ ዕጣ ከወጣ ከሶስት ወር በኋላ ለሚቀርብ የዕጣ አሸናፊ ቁጥር፣ ወይም

2) ለደረሰኙ የተሰጠውን ቁጥር ወይም የመሣሪያውን መለያ ቁጥር ለመለየት አስቸጋሪ በሆኑ ወይም አጠራጣራ በሆኑ ደረሰኞች ሽልማት አይሰጥም፡፡
3) አጠራጣሪ የሆኑ ደረሰኞችን በማጣራትም ተገቢው ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## 13. የሽልማት ወጪ አሸፋፈን

ሽልማት ለሚያስገኝ ደረሰኝ ዕጣ አሸናፊ የሚሰጥ ሽልማት ወጪ ከመንግስት በሚፈቀድና በሚመደብ በጀት እንዲሁም ከልዩ ልዩ ገቢ ይሸፈናል፡፡

## 14. በውክልና ስለማሠራት

1) የባለሥልጣኑ አግባብነት ያለው የሥራ ሂደት ይህን መመሪያ የማስፈፀም ኃላፊነት ቢኖርበትም ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ሥራውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያከናውንለት ሊወክለው ይችላል፡፡
2) የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ለሚሰጠው አገልግሎት ስለሚከፈለው ክፍያ ከባለሥልጣኑ ጋር በሚያደርገው የስምምነት ሰነድ ይወሰናል፡፡

## 15. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ፀድቆ በሕዝብ ማስታወቂያ ከተነገረበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ------------------------ ቀን 2001 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር